# ይድረስ ለፖለቲካ ድርጅቶች

በቀና መጀምር ቀና ነውና፣
እስኪ ለጥረታችሁ በቅድሚያ ላቅርብላችሁ ምስጋና፣
ምንም ቢሆን፣ ለትውልድ ትምሳሌነትን አሳይታችኋልና።

የቅድመ-አያቶቻችንን ጋሻ አንግባችሁ፣
ለእማማ ኢትዮጲያችን ቃል ኪዳን ገብታችሁ፣
እንዳይደፈር ዳር ድንበሯ፣
ዝቅ እንዳይል ሰንደቅ ክብሯ፣
የወገን ብስሶት፣ ስቃይ በደል ከብዶችሁ፣
ረሃብ እንግልቱ፣
የፍትህ ማጣት ብሶቱ አንገሽግሿችሁ፣
ሌት ተቀን እንቅልፍ ነስቷችሁ፣
ሁሌም ፍግም ጥልም፣ ደፋ ቀና ትላላችሁ።
ይህ ሁሉ ታላቅ አስተዋጽኦ ነውና፣
አሁንም ደግሜ፣ እንደገና፣
ከልቤ እላለሁ፣ ይድረሳችሁ ወገናዊ ክብር ምስጋና።

ግና ግና፣
ለሰርግ አይበቃምና የቈጭቈጭ ሽምት፣
እስኪ ልብ ብላችሁ የእስካሁኑን የገበያ ዉሎ አጢኑት።
ለትግሉ ሂደት ለዓመታት፣ በሕይዎት፣ በደም እየከፈላችሁ፣
እስከዛሬ ግን "ውኃ መልስ ውኃ ቅዳ" የሆነ ያ ሁሉ ልፋታችሁ።

በሕግ አምላክ እንዳልል ሕግ የለምና፣
ልበል፣ በአገር አምላክ በእናታችን፣
በደም በዋኘው ሰንደቃችን፣
አስተዋይና ብስሉን፣
ረቂቅና ብሂሉን፣
የኢትዮጲያን ሕዝብ መልዕክት ስሙ፤ ምከሩ፤ ዝከሩ፤
ሰለጩነቀው ብሏልና "ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ"።

ድህነታችን ነው እንጂ የሰው ሰራሽ ቁሳቁስ፣
አይደለምና ነገሮችን የማገናዘብ ዕውቀት ማነስ፣
መጥበብ የአስተሳሰብ ምህዋር ስፋት አድማስ፣
ይልቁንስ የሕዝባችንን ፍላጎት ተገንዘቡት፣
ልብ ገዝታችሁ አዳምጡት፣
አጢኑት፤ መርምሩትና ተቀበሉት፤
በተግባርም አሳዩት።
ፍላጎቱ ነውና፣ <u>አንድነት፣</u>
በውርስ የተላለፈለት የእናት አገሩ እሴት።

ሰለዚህ፣ እባካችሁ፣
በአገር አምላክ በእናታችን፣
በደም በዋዥው ሰንደቃችን፣
አስተዋይና ብስሉን፣
ረቂቅና ብሂሉን፣
የኢትዮጲያን ሕዝብ መልዕክት ስሙ፤ ምከሩ፤ ዝከሩ፤
ሰለጨነቀው ብኋልና "ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ"።

ያው የተለመደው ነባር ችግር፣
ዳመና እያንዣበበ ዝናብ በጣለ ቁጥር፣
ቀደምት አባቶቻችን፣ ቅድመ-አያቶቻችን፣
የመላ-ምት ጅረቶችን፣
ወንዝና ሐይቆችን፣
ዋኝተው ተሻግረው፣
ዳገት ቁልቁለቱንም አቋርጠው፣
በዚያ ሁሉ ውጣውረድ <u>የአገር ወንዝ ውኃ ጠጥተው፣</u>
የፈረንጅን መምጫ መንገድ ግራ ቀኙን ቃኝተው፣
ዓይን ለዓይን ተነጋግረው፣
ገና ከሩቅ የተንኮሉን በር ዘግተው፣

በሁሉም የእምነት አባቶቻችን፣

የሃይማኖት አበው ተባርከው፣
በአገር ሽማግሌዎች ተመክረው፣
የመስማት የማዳመጥን ሰነ-ልቦና ተክነው፣
በደረሰባቸው ፈተና ላይ ከልብ መክረው፣ ዘክረው፣
አዎ! ከልብ መክረው፣ ዘክረው!
<u>በአንድነታቸው ላይ የመጣን ችግር ትብትብ ተንኮል ፈትተው፣</u>
ሁሌም አቸናፊ፣ ሁሌም ድል አድራጊ ሆነው፣

ይኸውና ዛሬ የምንኮራባትን፣
የእኛነታችን መግለጫችንን፣
ኩራት አለኝታችንን፣
የነፃነት ቀንዲላችንን፣
አቀጣጥለው አብርተውልን፣
ነፃ አገር፣ ብሩህ ሰንደቃችንን ለዓለም አሳውቀውልን፣
እንኖራለን መንፈሰ ኩሩ ሆነን።

ግና ግና አሁን፣

ያው ታሪካዊው ችግር ተመልሶ መጥቶ፣
በባንዳ የልጅ ልጅ አጋፋሪነት፣
በከርሳም፣ ሆዳም አገር ሻጭ አጎብዳጅነት፣
በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅና ምዕራብ ተንሰራርቶ፣
ረሃቡና ድርቁ ሰውን እየጨረሰ፣
ስደት ወጣቱን እያፈለሰ፣
ድንበር ለዳረጎት እየተቆረሰ፣
በጎሳ የዘር ጥላቻ፣ የወገን ደም እየፈሰሰ፣

ሕዝባዊ ጀግንነቱ፣
እምቢ እንጃ ባይነቱ፣
ፍጹም ለጥቃት አይበገሬነቱ፣

እያለ ሞልቶ፣ ተርፎ ተንሰራፍቶ፣
<u>አንድነት ብቻ በመላላቱ፣</u>
ይባስ ብሎም አልፎ አልፎ በመጥፋቱ፣
ይኸውና እግር ከዎርች ተከርችማለች እናት ነፃነት፣
ሰንሰለቱን ሰባብሮ በጣጥሶ የሚያላቅቃት፣
ልጇ አንድነት ወገን ቢጠራው አልደርስ ብሏት፤
አዎ! ልጇ አንድነት ወገን ቢጠርው አልደርስ ብሏት።!

ታዲያ የፖለቲካ ድርጅቶቻችን፣

የቁጭ ቁጭ ትግል የትም አላደረሰምና፣
በጥብቅ መርምሩት የትግላችሁን ጎዳና!!!
እባካችሁ፣
በአገር አምላክ በእናታችን፣
በደም በዋኘው ሰንደቃችን፣
አስተዋይና ብስሉን፣
ረቂቅና ብሂሉን፣
የኢትዮጲያን ሕዝብ መልዕክት ስሙ፤ ምከሩ፤ ዝከሩ፤
ሰለጨነቀው ብሏልና "ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ"።

አክባሪ ወገናችሁ፣
የትናየት አገር
January 19/2016